

ፀጋዬ ደብተራው

# ኢትዮጵያ

ሐምሌ 2004 በነጻ የሚሰራጭ


እሁድ

ሀማ ቱማ ተጋባዥ ገጣሚ ነበር፤ ታላቅ የግጥም ምሽት በበርሊን ከተማ

ገጽ 2

አርቲስቶች የምስጋና ደብዳቤ ተቀበሉ፤ ደጋፊ ኮሚቴው የመዝናኛ ዝግጅት አደረገ

ገጽ 2

«ባንዳዎች ወደ ዲሲ፤ኢትዮጵያውያን ወደ ዳላስ»

ገጽ 2

## ዜና ዘገባ

## ወያኔ ያስመረቃቸው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሥራ አጥ ሆኑ ፤
## አዋሳ ከተማ በተኩስ ስትናወጥ ሰነበተች፤
## የቃሊቲ እስረኞች ተደበደቡ፤

የወያኔ ቡድን በዘረጋው የተሳሳተ መርህ ግብር የሀገሪቱ ዜጎች ሥራ አጥ ሆነው ባሉበት በዚህ ወቅት በተለይ ከዩኒቨርስቲ የተመረቁ ወጣቶች ሥራ አጥተው በቀን ሠራተኛነትና በተራ ወታደርነት እየተሰማሩ እንደሚገኙ ከተለያዩ አቅጣጫ የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ።

የደረግን የአፈና አገዛዝ እንቃወማለን፣ ለሕዝቡም ነጻነት እናጎናጽፋለን፣ ረሃብንና ችጋርን እናስወግዳለን ብለን ትግል ጀመርን ያለው የነመለሰ ዜናዊ ቡድን ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ከደርግ አገዛዝ በባሰ ሁኔታ በሀገሪቱ የአምባገነናዊ ሥርዓቱን በሕዝቡ ላይ የጫነ ከመሆኑም በላይ ወጣቱን ሥራ አጥ አድርጎት ለከፋ ችግር ዳርጎት እንደሚገኝ የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ።

ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የዲፕሎማና የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂ ወጣቶች ሥራ አጥተው እየተንከራተቱ ከመሆኑም በላይ የዕለት ጉርስ አጥተው ለልመና እየተዳረጉ ያሉበት ሲሆን ይህንኑ ችግር ለመቋቋም ገሚሱ በቀን ሥራ ገሚሱ በተራ ውታደርነት ተሰማርተው እንደሚገኙ ከደረሰን ዘገባ ለማረጋገጥ ተችሏል።

በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ የዩኒቨርስቲ ምሩቃን ወጣቶች ሥራ አጥተው እየተንከራተቱ የቤተሰቦቻቸው ሸክም በመሆናቸው እየተበሳጩ በስምንተኛ ክፍል ካርዳቸው ወታደርነት እየገቡ በተለያዩ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፖች እየሰለጠኑ ሲሆን እውቀት እና ትምህርት የሌላቸው ፣ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ድውይ የወያኔ ካድሬዎች ግን በተንጣለለ ቢሮ የደለበ ደመወዝ እየተከፈላቸው ይገኛሉ ሲሉ ወጣቶቹ በቁጭት ይናገራሉ።

ዛሬ የወያኔው አምባገነን ቡድን በመላ ሀገሪቱ ዜጎች ላይ በሚያደርሰው የከፋ ግፍ የተነሳ ብዙዎቹ ለስደት እየተዳረጉ ሲሆን የስደቱን እደል ያላገኙት የዩኒቨርስቲ ምሩቃን ደግሞ የወያኔ አባል ባለመሆናቸው ሥራ አጥ ሆነው እየተንከራተቱ ነው።

የወያኔ አባል የሆኑ በሉብሉብ ከዩኒቨርስቲ የተመረቁ ወጣቶች ከሕዝብ ካዝና ገንዘብ እየተሰጣቸው ከችሎታና ከውቀታቸው በላይ የሆነ ሥራ ተሰጥቷቸው በሕዝብና በሀገር ሀብት እየተጫወቱ ሲሆን በትምህርት ቤት ጎበዝ የተባሉ ነገር ግን የወያኔ አባል ባለመሆናቸው ብቻ ሥራ ተነፍጓቸው እየተንከራተቱ ወይም አማራጭ በማጣት በተራ ወታድርነት እየተቀጠሩ ይገኛሉ።

በተያያዘ ዜና ባሁኑ ወቅት በኑሮ ውድነቱ፣ በችግሩና በችጋሩ፣ አልፎ ተርፎ ሙብቱ ተገፎ በዘረኝነትና በፖለቲካ አድልኦ እየተሰቃየ የሚገኘውን ዜጋ የተለያዩ ሰበቦች እየለጠፉበት ለእስር እና ለመከራ የዳረጉት ከመሆኑ በተጨማሪ በጥይት እየገደሉት እንደሚገኙ ከተለያዩ ሥርፍራዎች የደረሰን ጥቆማ ገልጿል።

ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ ዕለት ሰኔ 9 ቅን 2004 ዓ.ም በአዋሳ ከተማ ነጋዴዎችና ፌዴራል ፖሊስ መሀከል በተከሰተ ግጭት አምስት ሰዎች ሲገደሉ ብዙዎቹ ደግሞ ቆስለው ሆስፒታል መግባታቸውንም ከደረሰን ጥቆማ ለማውቅ ተችሏል።

በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ታጣቂዎች በየቦታ ከሕዝቡ ጋር ፍልሚያ እያደረጉ ሲሆን እነዚህ ታጣቂዎች ፋሽስቱና ወራሪው የጣሊያን ጦር ያልፈፀመውን አስከፊ ጭፍጨፋ በዜጎች ላይ ያለ አንዳች ርህራሄ እየፈጸሙ መሆናቸው ከተለያዩ ቦታዎች ከሚደርሱን ዘገባዎች ለማወቅ ተችሏል።

ሽብር ፈጣሪው የወያኔ ቡድን በአዋሳ ከተማ ድንገት በፈጠረው ተኩስ ከተማዋ ስትናወጥ የሰነበተች ሲሆን የውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር በፍርሃት ተውጠው ከከተማዋ ሲሸሹ እንደታዩ በስፍራው የነበሩ የዓይን እማኞች ጠቁመዋል።

ወያኔ በቅርቡ ባወጣው አዲስ መመሪያ

ገጽ 3







# ኢትዮጵያ

## በኢሕአፓ የዲሲ ሪጅን ደጋፊ ኮሚቴ

## የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ


አድራሻ 5309 Georgia Ave. NW. 2nd fl. Washington DC 20011
ስ/ቁ 202 291 4217 ኢሜል dc.region.eprp@gmail.com

## ርዕሰ አንቀጽ

### የዛሬዉ ፈተና የመጻኢዉ በጎአችን መቅድም ነዉ

የኢትዮጵያ ሰማይ ለዉጥ አርግዟል ። የሕዝባችን ብሶት ጣሪያ ነኪቷል ። በሀገሪቱ ዉስጥ በአራቱም ማዕዘናት እዚህም እዚያም የአመጽ እሳት ምልክቶች ይታዩ ጀምረዋል ። ከመቼዉም ጊዜ በላይ ዛሬ የስርዐት ለዉጥ አስፈላጊነት ሕዝባዊ ግንዛቤን አግኝቷል ። ዘረኛዉና አምባገነናዊዉ አገዛዝም ከእንግዲህ በኋላ በዴሞክራሲ ስም ሕዝብንና ዓለምን እየደለለ መዝለቅ እንደማይችል ተረድቶታል ። በመሆኑም ወደ ተፈጥሮአዊዉ ባሕሪዉ ተመልሶ አፈናንና ግድያን የሙጥኝ በማለት የመከራችንን ዘመን ለማርዘም በመቅበዝበዝ ላይ ነዉ ።የአበዉ ብሂል "ከጎበዝ ተጣልቶ አያድሩም ተኝቶ ፤" እንዲል ዘረኛዉ ጸረ ኢትዮጵያ ሀይል የተገገርዉ ሕዝብ ቁጣ እየበረታበት፤ በሥልጣን የመቆዩቱ ነገር ይበልጥ አጠራጣሪ እየሆነበት በሄደ መጠን ሕዝብን በመከፋፈልና ከኑሮ በማፈናቀል ተለምዶዉ ይበልጥ ይገፋበታል ።ይህም በፈንታዉ ለማይቀረዉ ዉድቀቱ የተያያዘዉን የቁልቁለት ሩጫ የሚያፋጥን ሁነት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነዉ ።ከእንግዲህ ጥያቄዉ የጊዜና የሚከፈለዉ መስዋዕት ክብደትና ቅልለት ደረጃ ካልሆነ በቀር ሕዝባዊዉ ትግል ዘረኛዉን አምባገነናዊ አገዛዝ መንግሎ የመጣሉ እዉነታ አይቀሬነት ገሃድ ወጥቷል ።

በዚህ መልኩ ሀገራችንና ሕዝቧ አራት አሥርት በተጠጋ ዕድሜ ለሶስተኛ ጊዜ ከታሪክ መስቀለኛ ጎዳና ላይ ቆመዋል ። ከንጉሣዊዉ እስከ ወታደራዊዉ ደርግ ፤ከዚያም እስካሁኑ የወያኔ አገዛዝ የተደረገዉ ሽግግር ከአንዱ የጥፋት አዙሪት ወጥቶ ወደዘቀጠዉ የዉርደት አዙሪት ከመግባት ጋር የሚመሳሰል ነዉ ።ለተሻለ ሕይወትና ማሕበራዊ ስርዓት የተደረገዉ ትግል ከፍተኛነት ከተገኘዉ ዉጤት ጋር ከቶ አይገጥምም ። በሕይወት ከተከፈለዉ መስዋዕት ክብደት አንጻር ዕጣችን ከአንዱ ጨካኝ አምባገነን ጠጫ ተገላግሎ ከሌላዉ አረመኔአዊ የዘረኞች አገዛዝ ቀንበር ስር መዉደቅ መሆኑ የሚያሳዝን ነዉ ። ዛሬም ረሃብ ፤ ዛሬም ድህነት የኢያሌዎች፣ ዜጎች ኑሮ የተገደገደበት ካስማ ነዉ ። ዛሬም እንግልት ፤ዛሬም አፈና ፤ዛሬም ግድያ የዉሎ አዳራችዉ አንድ ገጽታ ነዉ ። የዘመናችን ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብሯ ያዘቀዘቀ ፤ ገናናዉ ታሪኳ ጥላሸት የተለወሰ ፤ ድንበሯ እያደር ወደመሐል የሚሸሽ፤ ቀጣይ አንድነቷም አደጋ የተጋረጠበት እንድትሆን ተደርጋለች ።የብሔራዊዉ ህልዉናዋ ቀጣይነትም ቢሆን ከአጠራጣሪነት የዘለለ አይደለም ። "ከድጡ ወደ ማጡ" ይሏል ይህ ነዉ ።

ለመጪዉ የሚበጅ ትምህርት ከቀሰምንበት ፤ ይህ ሁሉ መከራ ለነገዉ በጎአችን የተጻፈ መቅድም ነዉ ። ካለፈዉ ስህተቱ የማይማር ሕዝብ የለም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በተያያዘዉ ግብግብ ዘረኛዉን የወያኔ አገዛዝ ከነቅራቅንቦዉ አሽቀንጥሮ ከመጣል ወዲያ በምትኩ አቻናፊነቱን የሚያስረግጥበት፤ በራሱ ፈቃድ የሚያቆመዉን ሥርዓት መትከል ይጠበቅበታል። በደምና በነፍስ ግብር ጥቂት አፈ ጮሌዎችን ወይም አዳዲስ ሥዩመ ወያኔዎችን ከአራት ኪሎዉ መንግሥታዊ መንበር አደላድሎ በሆታ መመለስ ለዘመናት ለተጠናወተን መንግሥታዊ ልምሾ አብነት አያስገኝልንም ። የትግሉ ዲካ ፍትህና እኩልነት የረበበባት ፤ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመስረትና መገንባት ነዉ ። ለዚህ ዓላማ ስኬት በቀዳሚዉ ሰልፍ ሆኖ በቁርጠኛነት ከሚታገለዉ ሕዝብና ትግሉን ከሚመሩት ወገኖች ጎን በጽናት በመቆም የድርሻን ማበርከት ሀገሩን ከሚወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይጠበቃል ።

"ኢትዮጵያ" ጋዜጣችን የተወጠነችበት ዐቢይ መነሾም ከዚሁ አገራዊ ድርሻ ጋር የተሰናሰለ ነዉ ። ስያሜዋ በተሞካሸበት ሀገር በሚደረገዉ ሕዝባዊ ትግልና ታትማ በምትሰራጭበት የዋሽንግተን ዙሪያ በሚኖሩት የኢትዮጵያ ልጆች መሀከል የመረጃ መግከያ በመሆን ማገልገልን የበኩር ተልዕኮዋ አድርጓዋለች ። በዚህ ረገድ የመጀመሪያዉን ዕትም በረከት እነሆ ብለናል ። መልካም ንባብ ።

## ሀማ ቱማ

13ኛው አለም አቀፍ የገጣሚያን ፌስትቫል ከሰኔ አንድ እስከ ሰኔ 9/2012 በበርሊን ከተማ ተደረገ። በዚህ የግጥም ፌስቲቫል ላይ ኢኢትጵያዊው ገጣሚ ሀማ ቱማ ከአፍሪካ ገጣሚያን ተጋባዦች አንዱ ነበር። ይህ ፌስቲቫል በየአመቱ የሚደረግ ሲሆን፣ በዚህ አመት ዝግጅቱ ስፖንሰር የተደረገው በጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በአፍሪካን አካዳሚ አፍ አርትስ በርሊን፣ በሊትሬቸር አክሮስ ፍሮንቴርስ፣ በብሪቲሽ ካውንስል፣ በአውሮጳ ዩኒየን፣ በሌሎች የስነጽሁፍ ማእከሎች እና በኢምባሲዎች…ወዘተ ነበር።

ኢዛቤል ፈሪን አጉአር፣ ከዚህ በፊት የሀማ ቱማን እና የገጣሚ አለሙ ተበጀን የግጥም ስራዎች በማሳተሙ በኩል ሁኔታዎችን ያመቻቹ ሲሆኑ አሁን ደግሞ የአፍሪካ ገጣሚያን ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁለንተናዊ አስተዋጽዎ ያበረከቱ ሰው ናቸው።

ከሀማ ቱማ በተጨማሪ፣ በዚህ የግጥም ፌስቲቫል ላይ ሌሎች የአፍሪካ ገጣሚያን ተሳታፊ ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ፣ ፕ/ር ኢዩፍሬስ ኬዚላሀቢ፣ ታንዛኒያዊው ገጣሚ ጸሀፊና ፈላስፋ፣ ታዋቂዋ ገጣሚ ፣ አቀንቃኝ፣ የፊልም ተዋንያን የሆነችው ኬንያዊቷ ወ/ሮ ንግዋቲሎ ማዊዮ እና ግብጻዊቷ ገጣሚ እና ዘጋቢ ፋጢማ ናኡት ይገኙበታል። በዚህ ፌስቲቫል ላይ ታዋቂው ኬኒያዊ ገጣሚ በግል ጉዳዩ ምክንያት ለመገኘት ያልቻለ ሲሆን፣ ሱዳናዊው ገጣሚ አል ጻዲቅም በጉዞ መስተጓጎል የተነሳ በስፍራው ሊገኝ አልቻለም።

(ወደ ገጽ 4)

## አርቲስቶች

ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው ሂንስ ፖይንት የመዝናኛ ስፍራ ውስጥ፣በዋሽንግተን እና አካባቢው የሚገኙ የኢህአፓ ደጋፊዎች በመሰባሰብ አጠር ያለ ልዩ የመዝናኛ ዝግጅት አደረጉ።

በፈረንጆች አቆጣጠር ሰኔ 17/2012 በደተረገው በዚህ ዝግጅት ላይ፣የቀድሞ የድርጅቱ አባላት የነበሩ፣የኢህአፓ ድጋፊ ኮሚቴ አባላት ቤተሰቦች፣ሊሎች ተጋባዥ እንግዶች እና እንዲሁም በዋሽንግትን ዲሲ የኢህአፓ ከፍተኛ አመራር አባላት መገኘታቸውን ለማወቅተችሎል።

የመዝናኛ ዝግጅቱ የተጀመረው፣ከዚህ በፊት በተደረጉ የድርጅቱ የመዝናኛ ዝግጅቶች ላይ በፈቃደኝነት በመገኘት፣ታዳሚውን በሙዚቃ በማዝናናት አገልግሎታቸውን ላበረከቱ አርቲስቶች ምስጋና ለማበርከት ነበር። የምስጋናው ደብዳቤው የተበረከተው ከዲሲ ሪጅን የኢሕአፓ ኮምቴ ሲሆን፣ ደብዳቤውን ያበረከቱት አንጋፋዋ አርቲስት ወ/ሮ ጠለላ ከበደ ናቸው። ሽልማቱን ከተቀበሉት ውስጥ አንጋፋና ወጣት አርቲስቶች ይገኙበታል።

## «ባንዳዎች ወደ ዲሲ፤ኢትዮጵያኖች ወደ ዳላስ»

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ፣ በዳላስ የሚደረገውን አመታዊ የእግር ኳስ ውድድር በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሥነ ሥርአ ቱን በተሳካ ሁኔታ ልማጠናቀቅ ቅድመ ሁኔታዎችን ሁሉ መጨረሱን ካዘ ጋጅ ኮሚቴው ለመረዳት ተችሏል።

ይህንኑ የእግር ኳስ ውድድር ለመከታተል በተለያዩ ክፍለ ዓለማት የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በሥፍራው የደረሱ ሲሆን፣ ዳላስ እነዚህኑ እንግዶቿን በተሟላ መልኩ ለማስተናገድ ሽር ጉዱን አጠናቃለች ተብሏል።

በዚህ አመት የሚደረገው የዳላስ፣ ቴክሳስ የእግር ኳስ ውድድር የመክፈቻ ሥነ ሥነስርአት እሁድ ሀምሌ 1፣ 2012 ሲሆን፣ በሀምሌ 7፣ 2012 ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

ወደ ገጽ 4

## ዜና ዘገባ

መሰረት በሀገር ውስጥ የሚንቀሳቀስ እቃ ኮንትሮባንድ አይደለም ቢልም ቅዳሜ ሰኔ 9 ቀን 2004 ዓ.ም ግን ድንገት ሳይታሰብ በአዋሳ ከተማ የኮንትሮባንድ እቃ ይዘው ሲገቡ ተይዘዋል በሚል ምክንያት ከነጋዴዎች ጋር ግጭት ቀሰቀሶ አምስት ሰዎችን በጥይት ገድሎ በርካታዎችን ማቁሰሉ ተከትሎ በወያኔ የግፍ አገዛዝ ሆድ የባሰው የአዋሳ ከተማ ሕዝብ ግልብጥ ብሎ በመውጣት ሴት፣ ወንድ፣ አሮጊት፣ ሽማግሌ፣ ወጣት፣ ጎልማሳ፣ ሳይል ከፌዴራል ፖሊስና ከክልሉ ተወርዋሪ ፖሊሶች ጋር ፍልሚያ የገጠመ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቷል።በእለቱ በአዋሳ ከተማ በተከሰተው ግጭት በፖሊሶች ላይም ከባድ ጉዳት የደረሰ ሲሆን

በአሁኑ ወቅት በአዋሳ እና ዙሪያው ባሉ ቀበሌዎች ውስጥ ህዝቡ አመጽ በማንሳቱ የወያኔ መከላከያ ሰራዊት ዙሪያውን ከብቦ መቀመጡንና እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች እየተደረጉ ያሉት ተቃውሞች ከቀን ወደ ቀን እየሰፉና እያየሉ መምጣታቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

በ1994 ዓ.ም በአዋሳ ከተማ አቅራቢያ ሎቄ ተብላ በምትጠራው መንደር የዘንባባ ዝንጣፊ ይዞ ወደ አደባባይ የወጣውን የሲዳማ ብሔር ህዝብ በመትረየስ ያለአንዳች ርህራሄ ሲረሽን የነበረው ቡድን እንደ አዲስ አገርሽቶበት በመከላከያ ሰራዊት ጭምር ዜጎችን መረሸኑ ህብረተሰቡን አሳዝኗል።

በወቅቱ የደቡብ ክልል ርእሰ ብሔር ተብዬ በነበረው፣ በአሁኑ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ በኃይለማሪያም ደሳለኝ ትእዛዝ የተጨፈጨፉት ዜጎች ደማቸው ሳይድርቅ ፣ ስጋቸው ሳይረግፍ፣ አጥንታቸው ገና እርጥብ በሆነበት በአሁኑ ወቅት እንደገና በአዲስ መልክ በህዝቡ ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ ማድረጉ እጅግ አሳዛኝ እና የለየለት አውሬነት ነው ሲሉ የአዋሳ ከተማ ህዝብ በቁጭት እና በንዴት እየገለጹ መሆናቸውን የደረሰን ዘገባ ጨምሮ ገልጿል።

ሰሞኑን በአዋሳ ከተማ በኮንትሮባንድ ሰበብ የተጀመረው ግጭት ከዚህ በፊት የሲዳማ ህዝብ አንስቶ የነበረውን የመብት ጥያቄ በድጋሚ እንዲቀሰቀስ በመደረጉ በተከሰተ ፍጥጫ፣ በአሁኑ ወቅት አዋሳና ዙሪያዋ ብሎም ዲላ እና ይርጋለም እጅግ አስጊ ደረጃ ላይ በሚባል ውጥረት ውስጥ በመግባቱ በረሀ የከረመ ሰራዊት ወደክልሉ እየተጓጓዘ መሆኑንም ከአይን እማኞች ጥቆማ ማወቅ ተችሏል።

በሌላ ዜና በቃሊቲ እስር ቤት ለአምስት ቀናት የረሀብ አድማ ሲያደርጉ የነበሩት የፖለቲካ እና የህሊና እስረኞች ሰውነታቸው እየደከመና እራሳቸውን እየሳቱ በመምጣታቸው የተነሳ ሌሎች እስረኞች ጥያቄያቸው ይመለስ በሚል ተቃውሞ በማሰማታቸው በተፈጠረ ግጭት ግቢው በተኩስ ሲናወጥ መዋሉን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ይገላጻል።

የህሊና እና የፖለቲካ እስረኞች እንደማንኛውም እስረኛ ቤተሰቦቻቸው በተፈቀደው ጊዜ እየገቡ እንዲያዩን፣ የህግ አማካሪዎችም እንዲጎበኙን፣ ምግብና መኝታችን እንዲስተካከልልን፣ በግቢው ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ሙያዎች እውቀታችንን እንድናካፍል ይፈቀድልን፣ መጽሔቶች እና ሬዲዮኖች እንዲገቡልን፣ የሚሉ ጥያቄዎችን ለቃሊቲ እስር ቤት ሹሞች አቅርበው ምላሽ በመነፈጋቸው የአምስት ቀናት የረሀብ አድማ አድርገው የነበረ መሆኑ ታውቋል። የነዚህ እስረኞች ሰውነት መዛልና መዳከም የተመለከቱ አብረዋቸው የነበሩ ሌሎች እስረኞች የቁጣ ተቃውሞ በማሰማታቸው የቃሊቲ እስር ቤት ፖሊሶች በእሩምታ ተኩስ እንዲበተኑ ያደረጉአቸው ከመሆኑም በላይ ሁለት እስረኞችን በጥይት መትተው እንዳቆሰሏቸውም ከዜና ምንጫችን ዘገባ ማወቅ ችለናል።

ቅዳሜ ሰኔ 9 ቀን 2004 ዓ.ም በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ በተከፈተው ተኩስ ግቢው ሲናጥ የዋለ ከመሆኑም በላይ፣ ለጥየቃ በግቢው ውስጥ የነበሩ ቤተሰቦቻቸው በአስቸኳይ እንዲወጡ ተደርጎና ግቢው ተዘግቶ፣ የወያኔ ዘበኞች ዞን ሶስት ተብሎ በሚጠራው እስር ቤት ውስጥ ታስረው የነበሩትን እስረኞች በጀርመን ሰራሽ ዱላ እና በባህር ዛፍ ቆመጥ እጅግ ዘግናኝ የሆነ ድብደባ የፈጸሙባቸው መሆኑንና በድብደባውም ብዙዎቹ መጎዳታቸውን በተጨማሪ ለማወቅ ተችሎል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ እና የህሊና እስረኞች፣ «እስር ቤቶች ማሰቃያ ሰፍራ መሆኑ ያብቃ» በሚል በየእስር ቤቱ ውስጥ በእስረኞች ላይ የሚፈጸመውን ዘግናኝ ግፎች በመቃወም ባወጡት የአቋም መግለጫ መቃወማቸው ታወቀ።

ከቃሊቲ እስር ቤት ከሚገኙ የህሊና እስረኞች የቀረበ ጥሪ በሚል የተበተነው መግለጫ፣ እስር ነጥቦችን የያዘ ሲሆን፣ እስር ቤቱ የአንድ ብሄር የሆኑ ሰዎች የበላይነት የተያዘ መሆኑን እና ሥርአቱ አሁንም ከዘረኝነት ያልጸዳ መሆኑን ጠቅሶ፣ በአስቸኳይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ይጠይቃል።

በቃሊቲ እስር ቤት በተፈጠረው ድብደባና ወከባ የተንሳ፣ ብዙዎች የአልጋ ቁራኛ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በቂ ህክምና እንዳያገኙ በምደረጋቸው፣ ለከፋ ስቃይ እየተዳረጉ መሆኑንም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሏል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የወያኔው ሥርአት መዳከም ያስደነገጣቸው እና ያሳሰባቸው የቀድሞ ታጋይ የአሁኖቹ የህወሀት መኮንኖች፣ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው እንዲመደቡ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ባለፈው ሳምንት ከነጓዛቸው እና ቤተሰቦቻቸው የተሸኙ መሆኑ ታወቀ።

በቃሊቲ እስር ቤት፣ በዝዋይ እና በሸዋ ሮቢት ይኖሩ የነበሩ የህወሀት መኮንኖች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወያኔ ውስጥ ያለውን ትርምስ እና ሽኩቻ በመፍራት ብቻ የዝውውር ጥያቄ አቅርበው የነበረ ሲሆን፣ ባለፈው ሳምንት ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ትግራይ ክልል መሸኘታቸው የቃሊቲ እስር ቤት ምንጮች ገለጹ።

ከ70 በላይ የቀደሞ የህወሀት ታጋዮች የአሁኑ መኮንኖች የዝውውር ጥያቄ አቅርበው የነበረ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ፣ በጠየቁት መሰረት ለሁሉም የተፈቀደ ቢሆንም፣ 45 ያህሉ አስቀድመው ለመሄድ በመቻኮላቸው ሀሙስ እለት ሰኔ 8 ቀን 2004 ዓ.ም በሁለት አውቶቡስ እና የጭነት መኪኖች እቃዎቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ጭነው ትግራይ መቀሌ መግባታቸውን ምንጮች አስረድተዋል።

ጥቂቶች ደግሞ፣ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው አንሄድም በማለታቸው ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ለመሄድ እንደተገደዱ የጠቆሙት ምንጮቹ፣ የዝውውር ጥያቄው መልስ ካገኘ በኋላ ለመሄድ ፈራ ተባ እያሉ መሆኑን ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል።

## ተስፋ አልባ

በተስፋ የሚኖር በምኞት ይሞታል
ሳይተኛ የተኛም ሲነቃ ይወድቃል
በሀሳብ ዘመቻ ጦር የመዘዘውን
የቃላት አዳፍኔ ካውሬ አያድነውም።
የምላስ ጦረኛ የሰፋ ላይ ፋኖ
ጥይት የጮኸ ለት አይገኝም ከቶ።
ግራ ቀኙን ተቺ ተግባር አልባ ጮሌ
ሰሚሚ ጠዛ ነው አያመች ለወሬ።
ለፈረንጅ ያደረ ያንድነት አርበኛ
የእናጅሬ ወንድም የክህደት ሱሰኛ
ባንዳነት ባንጎሉ ሲሾር የቀረ ነው
ለአንድነት መጋኛ መሆኑ አይቀሬ ነው።
አይኑን ከፍቶ  ሚቃዥ ርግማን የሚያልም
ትግል ጠና ቢሆን ከቶ አያስገርምም ።
በተስፋ የሚኖር በምኞት ይሞታል
አጉል መፋዘዝን ቀንበርን ያጠብቃል።
ይህ ሁሉ ሀቅ ነው ወይስ አጉል ግራ
ምን ይፈይዳል ሰው አለተስፋ ጮራ?
ከጨለማው አልፎ ብርሃን ማይታየው
ሀቅን የተረዳ አይኑን የከፈተ
ወይስ
ተስፋ አልባ በድን በቁሙ የሞተ?

ሀማ ቱማ
ሐበሸኛ

# ሀማ ቱማ

13ኛው አለም አቀፍ የገጣሚያን ፌስትቫል ከሰኔ አንድ እስከ ሰኔ 9/2012 በበርሊን ከተማ ተደረገ። በዚህ የግጥም ፌስቲቫል ላይ ኢኢትጵያዊው ገጣሚ ሀማ ቱማ ከአፍሪካ ገጣሚያን ተጋባዞኙች አንዱ ነበር። ይህ ፌስቲቫል በየአመቱ የሚደረግ ሲሆን፣ በዚህ አመት ዝግጅቱ ስፖንሰር የተደረገው በጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በአፍሪካን አካዳሚ አፍ አርትስ በርሊን፣ በሊትሬቸር አክሮስ ፍሮንቱርስ፣ በብሪቲሽ ካውንስል፣ በአውሮጳ ዩኒየን፣ በሌሎች የስነጽሁፍ ማእከሎች እና በኢምባሲዎች…ወዘተ ነበር።

ኢዛቤል ፊሪን አጉአር፣ ከዚህ በፊት የሀማ ቱማን እና የገጣሚ አለሙ ተበጀን የግጥም ስራዎች በማሳተሙ በኩል ሁኔታዎችን ያመቻቹ ሲሆኑ አሁን ደግሞ የአፍሪካ ገጣሚያን ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁለንተናዊ አስተዋጽዎ ያበረከቱ ሰው ናቸው።

ከሀማ ቱማ በተጨማሪ፣ በዚህ የግጥም ፌስቲቫል ላይ ሌሎች የአፍሪካ ገጣሚያን ተሳታፊ ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ፣ ፕ/ር ኢዩፍሬስ ኬዚላህቢ፣ ታንዛኒያዊው ገጣሚ ጸሀፊና ፈላስፋ፣ ታዋቂዋ ገጣሚ፣ አቀንቃኝ፣ የፊልም ተዋንያን የሆነችው ኬንያዊቷ ወ/ሮ ንግዋቲሎ ማዊዮ እና ግብጻዊቷ ገጣሚ እና ዘጋቢ ፋጢማ ናኡት ይገኙበታል። በዚህ ፌስቲቫል ላይ ታዋቂው ኬኒያዊ ገጣሚ በግል ጉዳዩ ምክንያት ለመገኘት ያልቻለ ሲሆን፣ ሱዳናዊው ገጣሚ አል ጸዲቅም በጉዞ መስተጓጎል የተነሳ በስፍራው ሊገኝ አልቻለም።

# ባንዳዎች

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በወያኔ አዘጋጂነት እና በሼክ ሞሐመድ አላሙዲ የገንዘብ ድጋፍ ሰጪነት፣ በዋሺንግተን ዲሲ፣ ከዳላሱ በተቃራኒ የእግር ኳስ ውድድር ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ከተለያዩ ምንጮች ለማወቅ ተችሏል።
ተለጣፊ በመፍጠር የታወቀው ወያኔ፣ አሁንም የተለያዩ የእግር ኳስ ቡድኖችን እና የሙዚቃ ባለሞያዎችን ካገርቤት እና ከተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች በገንዘብ ገዝቶ በማሰባሰብ ከጁላይ አንድ ጀምሮ ተመሳሳይ ውድድርር በማድረግ ፣የሕዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀይር እና ከዋናው የዳላሱ ጉዞ ለማስቀረት በርካታ መደለያ መንገዶችን ማዘጋጀቱን፣ ሁኔታውን በቅርበት የተከታተሉ ልጸውል።

የኢህአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢወክንድ)፣ በዚሁ የወያኔ የእግር ኳስ ውድድር ዝግጅት ላይ ህዝቡ እንዳይገኝ፤ በዋሽንግተን እና ባካባቢው ባሉ ከተሞች በመዘዋወር ናሪው ህኔታውን እንዲገነዘብ እና ኢጋርነቱንም ለኢትዮጵያዊያን ወገኑ እንዲያደርግ ከማሳሰቡም በተጨማሪ፣ በዝግጅቱ ላይ በሚገኙ ዘፋኞች ላይ መላው የአሜሪካ ኖሪ እቀባ እንዲያደርግ እንዲሁም በማንኛውም ዝግጅቶች ላይ እንዳይጋበዙ እንዲያድርግ፣ «ባንዳዎች ወደ ዲሲ፣ ኢትዮጵያኖች ወደ ዳላስ» በሚል በራሪ ወረቀቶችን በመበተንጥሪውን አስተላልፏል።

# አርቲስቶች

ሽልማቱን አርቲስቶቹ ከመቀበላቸው በፊት የድርጅቱ አባል የሆኑት አቶ መንበሩ አጠር ያለ የምስጋና ንግግር ካደረጉ በሁላ፣ ሽልማቱን ወ/ሮ ጠለላ ከበደ እንዲሰጡ በመጋበዝ ስነስርአቱ የተጀመረው ሲሆን፣ በስፍራው የተገኙት አርቲስቶች ሽልማቱን ከወ/ሮ ጠለላ እጅ አንድ ባንድ ሲቀበሉ፣ ላልተገኙት ደግሞ በተወካዮቻችው በኩል እንዲደርሳችውተደርጎል።

አርቲስቶቹም በበኩላቸው ሽልማቱን ከተቀበሉ በኋላ፣ ለተደረገላቸው ሽልማት አመስግነው፣ ወደፊትም ድርጅቱ በሚያዘጋጃቸው ስብሰባዎችና ማንኛውም ዝግጅቶች ላይ በመገኘት ሙያዊ አገልግሎታቸውን በደስታ ለማበርከት ፈቃደኛ መሆናቸውን በተወካያቸው በኩል ለታዳሚው ከመግለጻቸውም በተጨማሪም፣ በስፍራው አጠር ያለና በድምጽ ብቻ የታጀበ ሙዚቃ በማሰማት ታዳሚውን ለማዝናናት ችልዋል።

በዚህ ሁኔታ የተጀመረው የመዝናኛ ዝግጅት፣ በስፍራው በሚጠበሱት ምግቦችና ለመጠጥ በሚሆኑ ውሃና የለስላሳ ምጠጦች ታጅቦ፣ አባላቱ ያደርጉ የነበሩት በፍቅር የተሞላ የርስ በርስ መስተጋብር ከነበረው አስደሳች የአየር ሁኔታ ጋር ልዩ ትእይንት ፈጥሮ ቆይቶል። በጊዚው በስፍራው የነብሩ ወጣቶች በቴፕ ሪኮርደር በታጀቡ ባህላዊ ዘፈኖች ያደርጉት የነበሩት አገራዊ ውዝዋዚ ታዳሚውን ለጭር ጊዜም ቢሆን ማፍዘዙ አልቀረም።



በመጨረሻም፣ መዝናኛ ዝግጅቱን ያዘጋጁትን የድጋፌ ኮሚቴ አባላትን ጠይቀን እንደተረዳነው ከሆነ፣የዚህ አይነቱ ዝግጅት ዋና አላማ፣ በድጋፌ አባላቱ መካከል ያለውን ትስስር ማሳደግ እና መስተጋብሩም ከተራ የርስ በርስ ግንኙነት ባለፈ ወደ ቤተሰባዊ ትስስር ደረጃ ከፍ ከማድረግ ባሻገር ድርጊቱ ኢትዮጵያን ከወያኔ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት ለሚደረገው ትግል የበለጠ አስተዋጽዎ ሊኖረው እንደሚችል ያላቸውን እምነት በአጽኖት ከገለጹ በሁላ የዚህ አይነቱ ዝግጅት ወደፊትም በተጠናከረ መልኩ እንድሚቀጥል አረጋግጠውልናል።

# ድርጅትዎን በኢትዮጵያ ጋዜጣ ያስተዋውቁ !

**አድራሻ** 5309 Georgia Ave. Nw , Washington DC 20011

ስ/ቁጥር 202 291 4217 e-mail: dc.region.eprp@gmail.com

# ትላንትና

## ግርማቸዉ ለማ፤

# በማለዳ የጠለቀዉ የኢሕአፓ ኮከብ

ያላለፈበት የሕይወት መንገድ ከቶ አልነበረም ።አንድ ወቅት ላይ የተማሪዎች ማሕበሩ ፕሬዚዳንት ሲሆን የበቃ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ፤ የአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት መምህር ፤ግንባር ቀደም የሠራተኛዉ አደራጅና የላብአደሩ ማሕበር (ኢላአማ ) መስራች ፤ ማለፊያ ገጣሚ ፤ ፍቅርና አክብሮት የተቸረዉ ታጋይ የሕዝብ ልጅ ነበር -ግርማቸዉ ። ድፍረትና በራስ መተማመን የግል ተሰጥዖዎቹ ነበሩ። ለሰዎች ሁሉ ያለዉ ፍቅር ወሰን ያልነበረዉ የመሆኑን ያህል የገዛ ራሱን ቤዛ አድርጎ ለማሳለፍ የማያቅማማ ፤ በአገርና በሕዝብ ፍቅር ልቡ የነደደ ጀግና ነበር ። ምዝበራን በጽኑዉ የሚቃወም፤ በግፉአን ወገኖቹ ላይ የሚፈጸም ማንኛዉም በደል የሚያንገፈግፈዉ፤ ርህራሄንና ሰብዐዊነትን የተመላዉ ባህሪዉ ገና ከማለዳ የተማሪነት ዕድሜዉ አንስቶ ይንጸባረቁበት ነበር ።ከስድስት ጫማ አለፍ የሚለዉ መለሎ ቁመናዉ ግርማ ሞገስን ፤ ብስል ቀይ ሰልካካ ፊቱ ደግሞ ዐይነ ግቡዕነትን ያላብሱታል ። ዝምተኛነቱና እንደበተ ርቱዕነቱ ተነባብረዉ '' ሙች በተናገረ" ያስብሉታል ።ለጓደኛነት ይመረጣል ፤ ለትግል ጓድነትም ይመቻል። ይህም ከትንሽ ትልቁ ጋር በቀላሉ ተግባቢ ከመሆኑና ከማይደብር ተፈጥሮዉ ጋር ተጣምሮ እያሌ ተማሪዎችን በቀላሉ በመማረክ ወደ ሕዝባዊዉ የትግል ጎራ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ አስችሎታል ። ለቆመለት ዓላማ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ በታማኝነቱ ጸንቶ ዘልቋል ። በታመነበት ሕዝባዊ የትግል መስመር ቆሞ እስከ መጨረሻ ህቅታዉ በአልበገር ባይነት እየታገለም ወድቋል -ግርማቸዉ ።

ግርማቸዉ ከኢሕአፓ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ) ጋር የነበረዉ ግንኙነት የሚጀምረዉ ድርጅቱ ኢሕአድ በሚል ስያሜ ምስራቅ ጀርመን ፤ በርሊን ላይ በ1964 ዓ.ም ከተመሠረተ በኋላ ነዉ ። በወቅቱ ባህር ማዶ የነበረዉ አመራር ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በመግባት ሀገር ቤት ከነበሩ የጥናት ቡድኖች ጋር ግንኙነት የጀመረ ሲሆን ለግርማቸዉም ስብስብ የዉህደት ጥያቄ አቅርቦለታል ። ወድያዉኑ መልስ ሳይሰጥ ጉዳዩን በጥሞና ሲመረምር የቆዩዉ ግርማቸዉ የኋላ ኋላ ከኢሕአድ ጋር ተዋህዷል ። የድርጅቱ የከተማ መዋቅር በተዘረጋበት ጊዜ የላቀ አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን በከተማ የጥቃት መከላከያ ክንፍ ዉስጥ ፤ በሠራተኛ አደራጅነትነትና የአዲስ አበባን በይነቀጠናን በመምራት ለድርጅቱ ዕድገትና ጥንካሬ የከፈለዉ ድርሻ የጎላ ነበር ።

በማርቆስ ሐጎስ ይመራ የነበረዉ የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር (ኢሠአማ) ከመስከረም 6 እስከ መስከረም 9 ቀን 1968 ዓ.ም ያደረገዉ ጉባዔና የደረሰባቸዉ ዉሳኔዎች ፤ እንዲሁም ጉባዔዉን ተከትሎ የተጠራዉ አገር አቀፍ የሥራ ማቆም አድማ ግርማቸዉና ጓዶቹ ባደረጉት ያላሰለሰ ጥረት የተገኙ ዉጤቶች ናቸዉ። በወቅቱ በሠራተኛዉ ማህበር ጽ/ቤት ተመድቦ ይሠራ የነበረዉ ግርማቸዉ ለማህበራቱ በአዲስ መልክ መደራጀት ግንባር ቀደሙን ሚና ተጫዉቷል። ከሠራተኛዉ መደብ ጋር የነበረዉ ጥብቅ ትስስር በዚህ ብቻ አያበቃም ። በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ላባደሮች መሪ፤ ወ/ሮ ዳሮ ነጋሽ መኖሪያ ቤት ዉስጥ ኢላአማ (የኢትዮጵያ ላብ አደሮች ማህበር) ለጠራዉ መስራች ጉባዔ ስኬት ግርማቸዉ ያደረገዉ አስተዋጽዖ ሚዛን የሚደፋ ነበር ። ወታደራዊዉ አገዛዝ እያደር በመጠናከር ላይ የነበረዉን የሠራተኛ እንቅስቃሴ ለመግታት ግድያንና እስራትን ያቃየጠ ርምጃ ወስዷል ። ግርማቸዉም በጥብቅ በመፈለጉ ሳቢያ ሕቡዕ ለመግባት ተገድዷል ።

መስከረም ላይ የጠባዉ አዲሱ የ1969 ዓመት ከቀደሙት የለዉጥና የትግል ዓመታት የተለየ መልክ ይዞ ብቅ አለ ። በግርማቸዉና ጓዶቹ የሚመራዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ ) በአባላት ብዛትና ጥራት እንዲሁም በድርጅታዊ አቅሙ ገዝፎ መታየቱ ሥልጣን ላይ የነበረዉን ደርግና በዙሪያዉ የተኮለኮሉትን ቅጥረኛ ሎሌዎቹን እንቅልፍ አሳጣቸዉ ። በዚህም ሳቢያ መንግሥታዊዉን ጉልበትና አስተዳደራዊዉን አዉታር በመጠቀም በኢትዮጵያ ምድር ከዚያ ቀደም ያልታዩ ሽብር በማስፈን ኢሕአፓን ለመደምሰስ ተንቀሳቀሱ ። ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል ተብለዉ የተጠረጠሩ ኢትዮጵያዉያን ያለፍርድ የሚታሰሩበት ፤የሚሰቃዩበት ፤ የሚረሸኑበትና የሚገደሉበት የሽብር ዘመን ተጀመረ ።ያ ዘመን ለኢሕአፓ አባላትና ግርማቸዉን ለመሳሰሉ መሪዎች በቀላሉ የማይወጡት ፈተና ደቅኖባቸዋል ። በፋሽስታዊዉ ጠላት እጅ ላለመዉደቅ በግል ከሚደረግ ጥንቃቄ በተጨማሪ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል በመምራት ላይ የነበረዉን ግንባር ቀደም ፓርቲ ከአደጋ መታደግ ፋታ የማይሰጥ ተግዳሮት ነበር ። ላባደሩን በማደራጀት ተግባር ላይ ከፊተኛዉ ረድፍ ተሠልፈዉ ይፋ በሚባል ደረጃ ሲንቀሳቀሱ ከፋሽስቶቹ ጥርስ ለገቡት ለነግርማቸዉ ደግሞ ከደርግና ከመረጃ አፈንፋኞቹ ራስን የመሰወሩ ነገር የተዐምር ያህል ከባድ ነበር ።

በ1969 ዓ.ም በወርሐ የካቲት ማብቂያ አካባቢ ከኢሕአፓ የአመራር አባላት መሀከል ብዙዎቹ የአዲስ አበባን ከተማ ለቅቀዉ ወጥተዋል ። አዲስ አበባ ከቀሩት ዉስጥ አንዱ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ ነበር ። በወቅቱ እዚያዉ ሆኖ የሚፈጽመዉ ድርጅታዊ ሥራ የነበረዉ መሆኑ ለመዘግዬቱ አንዱ ምክንያት ነበር ። በመሀሉ ፋሽስታዊዉ ደርግ ኢሕአፓን አስሶ ለመደምሰስ ዘመቻ ያቀደ መሆኑ በመረጃ ተደረሰበት ።የአዲስ አበባዉን ድርጅታዊ መዋቅርና በዉስጡም የነበሩትን አባላት በዚያን መሰሉ ቀዉጢ ሰዓት ጥሎ የመሄዱን ጉዳይ የዶ/ር ተስፋዬ ህሊና ፈጽሞ ሊቀበለዉ አልቻለም ።እዚያዉ ሆኖ ቀዉሱን ለመዋጋትና የሚመጣዉን መከራ ሁሉ ከሌሎቹ ጓዶቹ ጋር ለመካፈል በግሉ ቆርጦ ወሰነ ።

ግርማቸዉ ይህንን የዶ/ር ተስፋዬን ዉሳኔ በማግባባት ለማስቀየር ሞክሯል ። ሆኖም አዲስ አበባ ዉስጥ ለመቆዬት በቁርጥ የወሰነ መሆኑን በመረዳቱ፤ ባይሆን እንጦጦ አካባቢ ከሚገኘዉና የድርጅቱ አባል ከነበረዉ ከበሪሁን ማርዬ መኖሪያ ቤት አብሮት እንዲከርም ሃሳብ አቀረበለት ።ያ ቤት ለደህንነታቸዉ አስተማማኝ ይሆናል ተብሎ ይገመት ነበር ።

የአሰሳዉ ዘመቻ በተጀመረ ማግስት ግን በሪሁን የመኖሪያ ቤቱ መፈተሹ እንደማይቀርለት በመረዳቱ ቀዉጢዉን ጊዜ ለማለፍና ከተደቀነዉ አደጋ ለመዳን የሚያስችል የተሻለ ብልሀት እንዲፈልጉ ለዶ/ር ተስፋዬና ለግርማቸዉ አሳሰበ ።አያይዞም ፤በጊዜዉ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች የአሰሳዉ ዒላማ አልነበሩምና ፤ ወደ እርሱ ወይም ወደ ትዳር ጓደኛዉ ቢሮ ሄደዉ በመዋል የቀኑን አሰሳ እንዲያሳልፉና ምሽት ላይ አሳሾቹ ወደየመጡበት ከተበተኑ በኋላ ወደ ቤት እንዲመለሱ ሃሳብ አቀረበ። በሃሳቡ ላይ ተወያዩበት ። ዶ/ር ተስፋዬ ሃሳቡን አምኖበት ሲቀበለዉ ግርማቸዉ ግን ሳይስማማ ቀረ ። በሪሁንና ዶ/ር ተስፋዬ ሃሳቡን ሊያስቀይሩት ጥረት ቢያደርጉም አልተሳካላቸዉም ።በምትኩ ፤ በአካባቢዉ ወደሚገኘዉ ጫካ ሄደዉ ተደብቀዉ በመዋል ቀኑን በማሳለፍ አሳሾቹ ከተበተኑ በኋላ ወደ ቤት ቢመለሱ የተሻለ መሆኑን መከራቸዉ ። ግርማቸዉ ያለ መሣሪያ ትጥቅ ፤ ባዶ እጁን ወደ ከተማ የመመላለሱ ጉዳይ ከቶ ሊዋጥለት አልቻለም ።ረዥሙ ቁመናዉ ከሩቁ እንዳያሳጣዉና ለጠላቱ ምቹ ዒላማ ሆኖ ከእጃቸዉ እንዳይወድቅ የሰጋም ይመስላል ። በአንድ ሃሳብ መስማማት ባለመቻላቸዉ ሁሉም በየፊናቸዉ መንገዳቸዉን ቀጠሉ ።

ግርማቸዉ ከአንድ ሌላ የኢሕአፓ አባል ጋር በመሆን በአቅራቢያቸዉ ወደነበረ ዱር አመራ ። እዚያም ሳሉ ወደነበሩበት አቅጣጫ የሚመጡ ሰዎች ድምጽ ተሰማቸዉ ። በዚያን ዕለቱ የአሰሳ መርሐ ግብር ጥቂት ወታደሮችን የያዘ አንድ የዕዝ አሃድ የአካባቢዉን ጫካ እንዲፈትሽ አገዛዙ ትዕዛዝ ሰጥቶ ኖሯል ። ወታደሮቹ በጫካዉ ፍተሻቸዉ ወቅት አዲስ የሰዉ ዱካ በማግኘታቸዉ ተከታትለዉ ማነፍነፍ ጀመሩ ። በግርማቸዉ ግምት ወታደሮቹ በመቶ ሜትር ርቀት ነበር የሚከተሏቸዉ ። ቢሆንም ጫካዉ ጥቅጥቅ ያለ ነበርና አሳዳጆቹና ተሳዳጆቹ በዐይን ለመተያዬት አይችሉም ነበር ። ግርማቸዉ ሁለት በሳር ክፍክፍ የተከደኑ ጎጆዎች ከሚገኙበት ከአንድ ገላጣ ስፍራ እስኪደርስ ድረስ አንድ ሰዓት ሙሉ ያለማቋረጥ ተጉዟል ።

ከገላጣዉ ሥፍራ ከመድረሱ በአደን ላይ ስለሚያስፈልግ መሠረታዊ የክትትል ብልሃት ወላጅ አባቱ በአንድ ወቅት የነገሩት ታወሰዉ ። ታዳኙ እንስሳ አዳኙ እየተከተለዉ መሆኑን ነፍስ ካመጣዉ ጠረኑ አሽትቶ እንዳይለይ ከኋላ መከተልንና ከፊት መቅደምን ማስወገድ እንደሚገባና በምትኩ ከጎን ሆኖ መከተል እንደሚያዋጣ የሚያስገነዝብ ምክር ነበር ። ግርማቸዉ የአባቱን ምክር ወድያዉኑ በሥራ ላይ አዋለዉ ። በጉዟቸዉ ላይ ይከተሉት ከነበረዉ መንገድ በዘጠና ዲግሪ በመታጠፍ ከአሳዳጆቹ በስተጎን በሚገኘዉ ተቃራኒ አቅጣጫ ይገሠግሥ ጀመር ። ከአፍታ በኋላ አንድ ዙር ተኩስ ዙሪያ ገባዉን ሲያደበላልቀዉ ተሰማዉ ። ጉዞዉን ግን አልገታም ። በግምት አስራ አምስት ማይል ያህል ተጉዞ ከነበረበት ጫካ በተቃራኒዉ አቅጣጫ ወጣ ። ከጥቂት ማይሎች በኋላም ከአንድ የኢሕአፓ አባላት መጠጊያ ሥፍራ ለመድረስ ችሏል ። በኋላ ላይ መረዳት እንደተቻለዉ አሳሾቹ ወታደሮች ከገላጣዉ ሥፍራ ላይ የነበሩትን ሁለት የሣር ጎጆዎች በተኩስ አጋይተዋቸዋል ። የጎጆዎቹ ነዋሪዎች እርጅናና ድህነት የከበዷቸዉ ባልና ሚስት ሆነዉ ተገኙ ። ያን አጋጣሚ ተከትለዉ የባቱት ሁለት ወራት የተለወጠ ነገር አልታየባቸዉም ፤ አገዛዙ ግድያዉንና ማሳደዱን ገፍቶበታል ። እያንዳንዱ ቀን በግርማቸዉና በተቀሩት የኢሕአፓ አባላት ሕይወትና ደህንነት ላይ የተደቀነ አዲስ አደጋ ይዞ ብቅ ይላል ። 1969 ዓ.ም ሽብር ሕግ ሆኖ የተደነገገበት ፤ የትንቅንቅ ፤የፈተና ወቅት ነበር ። የ1969ኙ ሰኔ ደግሞ የፋሺስታዊዉ አገዛዝ የደህንነት መ/ቤት ምስጢር ለማነፍነፍ በስልክ ጠለፋ ሥራ ተወጥሮ የከረመበት ወር ነበር ። በዚሁ ወር አንድ ረፋድ ላይ ግርማቸዉ ለማ የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ከነበረ አንድ ጓድ ጋር ያደረገዉ የስልክ ዉይይት በአገዛዙ የደህንነት ክፍል መጠለፉ ታወቀ ። በዚሁ ሁነት መነሾ ግርማቸዉ ከአንድ ሌላ የድርጅት ሰዉ ጋር በተነጋገረበት ወቅት የኢሕአፓ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የሚኖሩባቸዉ ስልክ ያለባቸዉ ቤቶች በሙሉ እንዲለቀቁ በዚያኑ ሳምንት

ወደ ገጽ 7

# ነጻ ሀሳብ

## ለማጣፈጫ ሃገርን ወረራ!

በ1600ኛው መቶ ዓመታት ውስጥ የኢንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች በምዕራብ ኢንደስ (West Indies) እግራቸውን ሲያሳርፉ አላማቸው ትንበሆና ጥጥ ለሃገራቸው ፋብሪካዎች ለማቅረብ ነበር። ከነዚህ ደሴቶች ከሆነችው ባርባዶስ (Barbados) ላይ ከአረፉት ቅኝ ገዥዎች አንዱ ጄሚስ ዳራክስ (James Drax) የሚባለው በብራዚል ሃገር ሸንኮራ እንደሚሆን ካየ በኋላ በዚች ደሴት ላይ 1655 ዓ ም የሸንኮራ ተከላ ጀመረ። ተልኮውን `ለማጣፈጫ ፍላጋ'( needs for sweeter) በሚል ሰየመው። የሸንኮራ አገዳ ተከላ ለማጣፈጫ ፍለጋ ለምዕራብ ኢንዲስ (West Indies) ወይም በአሁኑ መጠሪያቸው ለካረቢያን (Caribbean) ሃገሮች መጥፊያቸው ሆነ። ሃገሬው ከአጽመ ርስቱ ተነቀለ። ያለ ክፍያ በቀለብ ብቻ ለቅኝ ገዥዎቹ በሸንኮራ ተከላውና ቆረጣው ላይ ተሰማራ። ቅኝ ገዥዎች የሃገሬው ጉልበት አልበቃ ብሏቸው አተላንቲክ ውቂያኖስን አቆርጠው ሩብ ሚሊዮን የሚሆኑትን አፍሪካውያንን ለባርነት ወደ ካረቢያን ሃገሮች እንደቃ በሰንሰለት ቀርቅበው በመርከብ ጭነው አመጧቸው። በባርባዶስ (Barbados) የተጀመረው የሸንኮራ ተካላ ወደ ጃሜካ (Jamaica) ሊዋርደ ደሲቶች (Leeward Islands) ተሰፋፋ። የኢንግሊዝ ዜጎች ከቀድሞ አባቶቻቸው የሰኳር ፍጆታ በስድስት ጊዜ ጨመረ። የካረቢያን (Caribbean) ሃገሮች መሬታቸውን አጡ፤ ባህል አልባ ሆኑ፤ የማንነት መገለጫው ዘፈንና ሩጫ ሆነ። ዛሬ በርስታቸው ላይ ሰፍረው የሚገኙት በባርነት ለሸንኮራ ተከላና ቆረጣ የመጡት አፍሪካውያን ናቸው።

ወደ ኋላ ተመልሰን ከአፍሪካ በባርነት ሰም የመጡቱን አፍሪካውያን ሁኔታ ስናየው እጅግ የሚሰቀጥጥ ነው። ትንሽ ጥፋት ካጠፉ ወይም ከበደሉ የተነሣ ለማመጽ ከተነሣሱ አለቀላቸው።ውኃና ምግብ ተነፍገው እንዲሞቱ ይደረጋሉ፤ የደከመው ሰውነታቸው ለውሻ ይቀርባል፤ እዚህ ከመድረሳቸው በፊት በእግር ብረት ይታሰራሉ፤ ይገረፋሉ፤ አካለ ሥንኩላን እንዲሆኑ ይደረጋል። የዚህ ሁሉ መነሻው የሰኳር ምርትን አሳድጎ ባለሐብቱ ተንደላቅቆ እንዲኖር የኢንግሊዝም ሕብረተሰብ የሰኳር እጥረት እንደይፈጠርበት ነበር።

በአሁንም ዘመናችን (Caribbean Sugar industry taken as a model of international exchange) በማለት ይወደሳል። ይታያችሁ በካረቢያ ሕዝቦች ላይ ለስኳር ተከላ ሲባል ሃገር አልባ የሆኑትን እንደጥሩ ምሳሌ ይጠቀሳል።አህጉራዊ ንግድ (Globalization trade) የሚባለው ምስጢሩ ይህ ነው።

EthioLion Ethiopia Will Prevail! EthioLion.Com

መለስ ዜናዊም እንደጌቶቹ የኢትዮጵያ ገበሬ ከቀደሞ ይልቅ አሁን የሰኳር ተጠቃሚ ሆኗል እያለ በማሰብ ችሎታችን ላይ ያሾፋል። በግልባጩ ገበሬውን ከርዕስቱ እየነቀለ በሕጋዊነት ሕገወጥ ተግባር እየፈጸመ ይገኛል። እስከ መቼ ይቀጥላል?

በነፃነቷ ኮርታ በጀግኖች ልጆቿ ተከብራ ቅኝ ገዥዎችን አሣፍራ የኖረች ሃገራችን በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በአህጉራዊ ንግድ (Globalization) ስም ተደፍራለች። ዘርን መሠረት ያደረገው በትግራይ ክፍለ ሃገር በስልሳዎቹ አጋማሽ እንቅስቃሴ የጀመረው ቡድን ኢትዮጵያን ለባዕዳን ከበርቴዎች ለሽያጭ አቅርቧታል።

የትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባር ኢትዮጵያን በማስተዳደር ስም ለባዕዳን ሃገሪቱን እየሸጠ ይገኛል። ምንም እንኳን አንድ ሃገር ሉዐላዊነቱን ለማስጠበቅ የመከላከያ ኃይል አስፈላጊ ቢሆንም የኢትዮጵያ ሠራዊት ለዚህ በቂ ሆኖ አልተገኘም። ለባዕዳን ጥቅም አስጠባቂ መሆኑን በጋንቤላ፣ በዋልድባ፣ በአፋር፣ በኦጋዴን፣በአርሲ፣ በወለጋ፣ በከፋ፣ በሻኪሶ መሬታችን ለሸንኮራ ተከላ ለባዕድን አይሰጥብንም በማለታቸው በሃገሬቱ ሰም የተዋቀረው የመከላከያ ኃይሉ በአጋዚ ሠራዊት ሰም ሕዝቡን እያጠፋ ነው።

የወቅቱ መንግሥት በቁንጮው መለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራይን ልጆች በዘር ሐረጋቸው አታሎ፤ ከተራ ወታደር እስከ ጀነራል በሚደርስ የማዕረግ እርከን ፤ ከእግር ጥፍራቸው እስከ ፀጉር ጫፋቸው አስታጥቆ በአጋዚ ስም መሬቴን ለባዕዳን አሣልፌ አልሰጥም ያለውን ሕዝብ ያስጨርሳል።ይህ ሠራዊት ማሰብ ያለበት በአፍሪካዊያኖችና በካረቢያን (Caribbean)ሃገሮች ላይ የደረሰውን ዓይነት ውርደት በልጅ ልጆቹ ላይ እንደሚደርስ ከአሁኑ መገንዘብ አለበት። በዘር አሻከላ ወጥመድ ተተብትቦ በማዕረግና በጥቅማጥቅም ተወጥሮው ዛሬ ቢታይ መጭው ትውልድ ያፍርበታል። የልጅ ልጆቹ ሲወቅሱት ይኖራሉ። የሚታየውን አላየሁም ብሎ ቢክድ ደግሞ የቁም ሞት ነው።

ወታደሩ ሲቪሉም ተማሪው መምህሩ መላው የሃገሬ ሕዝብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በሃገራችን ላይ በልማት ስም ያጃበበውን የውርደት ስንቅ ነገ ዛሬ ሳንል ማስቆም አለብን። የወያኔ ልማት ይዞ የሚመጣው ውርደት ነው፤ በአፍጫችን ይውጣ። ደማቸውን እያፈሰሱ ያሉት ወገኖቻችን ለልጅ ልጆቻችን መሆኑን ተረድተን አብረናቸው እንቁም። በካረቢያን ሃገሮች የደረሰው ውርደት እንዳይደርስብንም መነሣቱ ዛሬ ነው።

ሰው በሃገሩ
ሰው በወንዙ
ቢበላ ሣር ቢባላ መቅመቆ
ይከበር የለም ወይ! ማንነቱ ታውቆ
ኢትዮጵያ ሃገራችን ከውርደት በቆራጥ ልጆቿና በእግዚሐብሔር ኃይል ትድናለች!

EthioLion Ethiopia Will Prevail! EthioLion

ዉስጥ መመሪያ አስተላልፎለት እንደነበረና የአዲስ አበባዉ በይነቀጠናም ተመሳሳይ ርምጃ እንዲወስድ ትዕዛዝ የወረደለት መሆኑን ሰምቷል ። ግርማቸዉ ግን በመመሪያዉ መሠረት መኖሪያ ቤቱን ለቅቆ ለመዉጣት ፈቃደኛ አልነበረም ። በዚያኑ ዕለት በተፈጠረ ሌላ አጋጣሚ ሰበብም መኖሪያ ቤቱን መልቀቅ እንደሚኖርበት በግል ተነግሮታል ። ልበ ሙሉዉ ግርማቸዉ ግን አላደረገዉም ።

የስልክ ጠለፋዉ ዕቅድ በታወቀ በጥቂት ሰዐታት ዉስጥ የአገዛዙ ልዩ የደህንነት ሀይል በአሥራ ሶስት የኢሕአፓ ቤቶች ላይ ወረራ ፈጸመ። ከእነዚህ ቤቶች አንዱ የአዲስ አበባዉ በይነቀጠና ኮሚቴ ዋና ጽ/ቤትና የግርማቸዉ ለማ መኖሪያ ነበር ። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሁለት የአብዮት ጥበቃ አባላት ወደ ቤቱ መጡ ። የቤቱን ነዋሪዎችም የበረንዳቸዉን መብራት እንዲያበሩ አዘዙዋቸዉ ። ግርማቸዉና አስፋዉ የሚባል ሌላ የበይነቀጠናዉ ኮሚቴ አባል ከቤቱ ወጥተዉ በጥድፊያ ወደ መኪናቸዉ አመሩ ። በመንገዳቸዉ ላይም ቤቱን ለመዉረር ዝግጅት ላይ የነበሩ አያሌ የደህንነት መኮንኖች ቦታ ቦታቸዉን ሲይዙ ተመለከቱ ።

የደህንነቱ መኮንኖች እነግርማቸዉን እንደተመለከቱ ማንነታቸዉን ሊጠይቋአቸዉ ሞከሩ ። በዚህ ጊዜ ግርማቸዉ አላወላወለም ። ከመቅጽበት ሽጉጡን አዉጥቶ ተኩስ ከፈተ ።የተኩስ ልዉዉጡ ግማሽ ሰዓት ያህል ፈጀ ። በመሀሉ ሁለቱ የኢሕአፓ ልጆች መኪናቸዉን ከቆመበት ትተዉ አመለጡ ። ወዲያዉኑም የደህንነቱ መኮንኖች ቤቱን ወረሩት ። በወቅቱ አሥራ አንድ የሚሆኑ የኢሕአፓ አባላት በዚያ ቤት ዉስጥ የነበሩ ሲሆን ሁሉም ሳይያዙ አምልጠዋል ።

ግርማቸዉና አስፋዉ ከተጋረጠባቸዉ አደጋ አምልጠዉ መርካቶ ሲደርሱ ከምሽቱ አራት ሰዓት አልፎ ነበር ።ከአንዲት ከቆመች መኪና ባለቤት ጋር ተስማምተዉ ሌሊቱን በመኪናይቱ ዉስጥ አሳለፉ ። ግርማቸዉ በማግስቱ ማለዳ ላይ የበይነቀጠና ኮሚቴዉ ለስብሰባ ሲጠቀምበት ወደ ነበረ አንድ ሌላ ቤት በመሄድ ሲያጣራ ቤቱ ለወረራ በዕቅድ ከተያዙት መሀከል አንደኛዉ መሆኑን ደረሰበት ። ወደሌላ ሥፍራ ከመሄዱ በፊት ግን ሁኔታዉን ለማጣራት ኮሚቴዉ ቀደም ብሎ ሲጠቀምባቸዉ ከነበሩት ቤቶች ወደ አንዱ ደጋግሞ ስልክ ደወለ ።ስልኩ መስመሩ መያዙን የሚገልጽ ምልክት እየሰጠ አስቸገረዉ ። መስመሩ ሆን ተብሎ እንዲቋረጥ የተደረገ መሆኑን የተገነዘበዉ ግርማቸዉ ከአስፋዉ ጋር በመሆን ካዛንቺስ ወደሚገኝ ሌላ ቤት አመራ ። ያም ቤት ተመሳሳይ ዕጣ ደርሶት ኖሮ የደህንነቱ ወታደሮች ከበስተዉስጥ አድፍጠዉ ከወጥመዳቸዉ የሚወድቅላቸዉን ሰለባ በመጠባበቅ ላይ ነበሩ ። አስቀድሞ ወደ ቤቱ የተጠጋዉ አስፋዉ በአጥሩ

ለላብአደሩ ትግልና ለዓላማዉ ባሳየዉ ታማኝነትና በከፈለዉ መስዋዕት በሠራተኞች ዘንድ የነበረዉ ፍቅርና አክብሮት ወሰን አልነበረዉም ። ግርማቸዉና ህያዉ ተግባሩ ምንጊዜም በኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል ታሪክ ዉስጥ እንደኮከብ ሲያበራ ይኖራል ። የተጋደሎዉ ድርሳንም በኢትዮጵያ ሠራተኞች ልቦና ተቀርጾ ለዘመናት ይኖራል ። ክብር ሞቱ ለሰማዕት ።



*ሀረርጌ ፤ አሰበተፈሪ ከተማ ዉስጥ ከቀኛዝማች ለማ ኪዳኔና ከወይዘሮ ዘቢደሩ ከወንድበላይ የተወለደዉ ግርማቸዉ ፤ አንደኛንና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃን ዕትብቱ በተቀበረባት ከተማ ስም በተሰየመዉ ት/ቤት ተምሯል ። በአምቦዉ የእርሻ ት/ቤት የከፍተኛ ሁለተኛ ትምህርቱን በስኮላርሺፕ በማጠናቀቅ ብሔራዊዉን ፈተና አልፎ ዩኒቨርስቲ በመግባቱ ወደ አዲስ አበባ አቅንቷል ። በዩኒቨርስቲዉ ቆይታዉ በቅድሚያ ሕክምና ለመማር ተመዝግቦ የነበረ ቢሆንም ትምሕርቱን ጨርሶ የተመረቀዉ ግን በሕግ ዘርፍ ነበር ።*

መግቢያ በር አጮልቆ ወደ ዉስጥ ሲመለከት በግቢዉ ዉስጥ የሚተረማመሱትን ወታደሮች ማየቱን ለግርማቸዉ አስታወቀዉ ። ወዲያዉኑም፤ ከተጠመደላቸዉ ወጥመድ ለማምለጥ ሩጫ ጀመሩ ። ሩጫቸዉን ያስተዋሉት የደህንነት መኮንኖችም ተከትለዉ ያሳድዷቸዉ ጀመር ። ግርማቸዉ ከጠላቶቹ ለማምለጥ አቅሙ የፈቀደዉን ሁሉ ቢያደርግም በተማሪነት ዘመኑ ጉዳት የደረሰበት ቁርጭምጭሚቱ እንደ ልቡ ለመሮጥ አላስቻለዉም ። በስተፍጻሜዉ ሽጉጡን አዉጥቶ ለመከላከል ቢሞክርም ጠላቶቹ በመሣሪያም በቁጥርም ብልጫ ነበራቸዉና ከትግሉ ሜዳ ግንባሩን ሳያጥፍ ወደቀ ።


የግርማቸዉ መሰዋት ለትግሉ በተለይም ለኢሕአፓ እጅጉን የከበደ ጉዳት ነበር ። ከኢሕአፓ አመራር አባላት አንዱ እንደመሆኑ በሕይወት ዘመኑ ለትግሉ ጥንካሬና ለድርጅቱ ዕድገት ያበረከተዉ ድርሻ ላቅ ያለ ነዉ ። ድርጅቱ ኢሕአፓ ችግር ዉስጥ በነበረበት በዚያ ፈታኝ ወቅትም ጽናቱንና ቆራጥነቱን በግብር ያስመሰከረ ጓድ ነበር ።

## ለእነ ፀጋዬ

ባልሰማ ይሻለኛል ሀቁ
ያ የደረሱበትን
ባልውቅ እመርጣለሁ የእነሱን ሰቆቃ
የአእምሮ ስእሌ ዋጋ እንዳያጣ
ባልሰማ እመርጣለሁ የሆኑትን
ስፈራ ስቸር ምገምተውን
አልስማ እውነታ ሀቅ ምትሉትን
ተስፋን በደረቅ መሬት ምትገሉበትን።
ይቅርብኝ ለእኔ ግምቴ
ይቅር ከእኔ ጋር ምኞቴ
ሞት ስቃዬን በሳቃቸው ረቱት ማለቴ
የሚውጣቸው ጉድጓድም
ሊቆፈር አይችልም ማለቴ

ሀማ ቱማ






1. የኢሕአፓ ደጋፊዎች በሄንስ ፖይንት የመዝናኛ ሥፍራ

2 ሀማ ቱማ በበርሊን ከተማ ግጥም ሲያነብ

